# አራራት

አራራት የኖኅ መርከብ ከጥፋት ውሃ በኋላ ያረፈበት የተራራ ስም ነው።

የሐመረ ኖኅ የሰንበት ት/ቤት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ይህችን በየ3ወሩ አንድ ጊዜ እየታተመች የምትወጣ ጽሑፍ አራራት በማለት የሰየመውም በዚህ ምክንያት ነው።


**ሕፃን ተወልዶልናልና ፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ፤ ስሙም ድንቅ መካር ፥ ኃያል አምላክ ፥ የዘላለም አባት ፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።** ትንቢተ ኢሳይያስ 9፥6

## የዓለም ጉብኝት በክርስቶስ

ዓለም የሚባለው የሰው ልጅ ያለበት መሬቱ ባሕሩ በውስጡም የሚገኘው ፍጥረት ሁሉ ነው። ከዚህም ውስጥ ንባብ፣ አእምሮ ያለው የዓለሙም ባለቤት ዓለምም የሚባለው የሰው ልጅ ነው። የሰው ልጅ ወዶ በሠራው ጥፋት ከአምላኩ ጋር በመጣላቱ ፍጥረቱ ሁሉ ተጠልቶ ይኖር ነበር። ስለዚህም ከሰማይ በታች ለርሱ ተስፋ የሚሆነው ነገር ባለመኖሩ ሲከላተም ወዶቆ ተረስቶም ይኖር ነበር። ክብርና ምስጋና ይግባውና አምላክ በባሕሪው ቸር ይቅር ባይም በመሆኑ ይቅር ሊለው ፈቀደና ከሰማይ ወርዶ ጐበኘው።

እግዚአብሔር አምላክ እኛ ሰዎች ጠላቶቹ ሰንሆን በልጁ ሞት ይታረቀን ዘንድ በልጁ ጐበኘን (ሮሜ 5፥7)። የእግዚአብሔር ጉብኝት የሰውን ታላቅ ፍጥረትነት ያሳያል፤ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ምንኛ እንደሚወደው ያመለክታል።

በአዳም በደል ምክንያት ዓለም ረክሶ ነበር፣ የሰውም ልጅ በራሱ ጥረት ሊድን አለቻለም ነበር፣ እንዲሁ ተረስቶ ቀርቶ ነበር፣ ክርስቶስ ፍጹም ሰው በመሆን የሰውን በደል ከኛ አራቀልን፤ እኛን አከበረን።

ይኽ መጎብኘት የሚባለው የክርስቶስ ሰው መሆን ሥጋን መልበስ ነው። የክርስቶስ ልደት የእኛ መጎብኘት ነው ።ልደቱን ስናከብር በልማድ ያለውን እንደኛ መወለድ አድርገን የምንመለከተው አይደለም።




ሰው ብዙ ተባዙ በተባለው መሠረት እያንዳንዱ እንዲሁ ይወለዳል፣ ያንን ከጨለማ ወደ ብርሃን የመጣሁበት ከጠባብ ማሕጸን ወደ ሰፊው ዓለም የመጣሁበት ጊዜ በማለት የልደቱን ቀን ያከብራል። እኛ የክርስቶስን ልደት ስናከብር ግን ከዚህ በተለየ ነው፤ ልደቱ የኛን መታረቅ ያመለክታል የኛን ከወደቅንበት መነሳታችን ያመለክታል። በጠቅላላም የዓለምን ድኅነት ያመለክታል፣ ታዲያ የክርስቶስ ልደት የኛን ስብእና፣ የኛን ነፃ መውጣት ስለሚያመለክት ክብሩ የተለየ ከፍም ያለ ነው።

በዚህ በልደቱ ጊዜ የኛንም ከመንፈስ መወለድ ልንገነዘብበት ደስታችን ከመብልና ከመጠጥ የተነሳ ሳይሆን ከፍ ያለ መንፈሳዊ ስሜት ሊኖረው ይገባል።

ያሬድ የተባለው ኢትዮጵያዊ ሊቅ «መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ» ሲል የጠፋውን ለማግኘት የሞተውን ለማስነሳት በአጠቃላይ ለሁሉቤዛ ለመሆን የመጣ መሆኑን ይገልጥልናል።የእግዚአብሔር ወደ ዓለም መምጣት የእግዚአብሔር ዓለምን መጐብኘት ለሰው ዘር ሁሉ ትምክህት ነው። አመጣጡን አምነን ብንቀበለው በእርግጥ ልጆቹ እንሆናለን፣

ዮሐንስ ወንጌላዊ ግን በጸጸት መልክ «ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም» በማለት ይናገራል(ዮሐ 1፥ 11)። በእርግጥ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ጐብኝቶናል፣ ፍጹም ድኅነት ያገኘነው በእርሱ ነው።

ገና፣ ልደት እያልን የምናከብረው በዓል የእግዚአብሔር መጎብኘት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የተዛመድንበት እግዚአብሔር እኛን ይቅር ብሎ ወገኖቹ ያደረገበት ጊዜ ነው። ይኽ ዕለት የሰው ክብሩ የተገለጠበት የሰው ልጅ አንገቱን ቀና አድርጎ ለመሄድ የቻለበት ነው።

ደስታችን በመዝሙር በማኅሌት በዘፈን እንገልጣለን፤ ይኽ የመቀበላችን ምልክት ይመስላል፣ ግን መዝሙሩ ማኅሌቱ የመቀበላችን ምልክት ይምሰል እንጂ መቀበላችንን ማመናችንን እንዴት ነው በስራ የምንገልጠው? ጌታችንን በሁሉ እንምሰለው፤ በእርምጃው እንከተለው፣ በጠቅላላው እኛነታችንን ለእርሱ እንስጠው፣ ህይወታችንን ከእርሱ ጋር እናርገው።

**አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ**

---

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

ካለፈው የቀጠለ......

### የዛጌ ዘመነ መንግሥት

በ912 ዓ.ም አካባቢ መራ ተክለ ሃይማኖት በትረ መንግሥቱን በኃይል ወስዶ፣ መንበረ መንግሥቱን ከአኲሱም ወደላስታ አዛውሮ ስመ መንግሥቱንም ዛጌ ብሎ ነገሠ። በዚህም የተነሣ የዛጌ ሥርወ መንግሥት ተብሎ ሲታወቅ ከዛጌ ጋር 11 የርሱ ወገኖች ነግሠዋል ፤ ይኸም ከ912 እስከ 1245 ነው። እነዚህ ነገሥታትም የክርስትና እምነት ይበልጥ ይስፋፋ ዘንድ ጳጳሳትን ከግብጽ እንዲመጡ በማስደረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

(ወደ ገጽ 3 ይዞራል)

## Celebrating the Twelfth Day of God the Incarnate

Today, as in the fourth century, when this feast appeared, together with the celebration of Christ's birth as an infant, there are many disputing how much of traditional Faith might still be relevant for modern man. St. John, the Baptizer of our Lord, dedicated his life to being just as attuned to God's revelation as the elements of nature prevailing in that wilderness where he lived and preached. Like the elements of water, rocks and beasts, he appreciated the real thing when He came along.

(Continued on Page 2)

## <u>የቃናዋ እመቤት</u>

ወይን ጠጁ ሲያልቅባቸው
የሚያደርጉት ሲጠፋቸው
መች ዝም አለች እናታቸው
እመብርሃን መውጫቸው
የዶኪማስ ባለውለታ
የአገልጋዮቹ ትዝታ
የእድምተኞቹ ሁሉ እርካታ
የሐዋርያት አለኝታ
የምልክቶች መጀመሪያ
ሲያደርጋት ልጇ አክብሮ
ለኛ እንድትሆን አዘክሮ
ሲለመነን በሳ ላይ አድሮ
ፈጥኖ ሰማት በአንክሮ
የቃናዋ እመቤት አማላጅዋ
የማይቋጠረው እርዳታዋ
የማይቆጠረው ስጦታዋ
የማይለካው ዋጋዋ
ልጆቼ ትለናለች
በፍቅሯ እየሳበች
በክንዷ እያቀፈች
ልታወጣን ከዓለም
ወድቀን እንዳንስጥም
ልትመራን ደግፋ
ልትሆነን የኛ ተስፋ
ልትታደገን እንዳንጠፋ
ከተፍ አለች ፈጣኗ
መላእክተ ብርሃንን አስከትላ
እየመራች ልታደርሰን
አይ እመቤቴ እሩኅሩኋ
መቼ ያልቃል ደግነቷ
ይፈውሳል መድኃኒቷ
ለአመነባት በአማላጅነትዋ
ተራው ውኃ ተለውጦ
ስም ተስጥቶት ጸበል ተብሎ
ዕውሩን እያበራ
ጎባጣውን እያቀና
አንካሳውን እያረታ
ለምጻሙን እያነጻ
ዲያብሎስን እየቀጣ
መግቢያ መውጫ እያሳጣ
የቃናው ውኃ ዛሬም አለ።
የድንግልን ትእዛዝ እየተቀበለ
እስከ ምጽአት ላይቋረጥ
ድኅነት ፈውስን ለኛ ሲሰጥ።

ከኃይለመስቀል ተስፋያ
ለንደን

## Celebrating the Twelfth Day ....

*(cont. from page 1)*

By contrast, even in early church history there were those supposing Jesus to have either been just a very specially blessed creature or a phantom that could only have appeared in history as physically human. And within recent history we behold thousands of attempts to either make an incomplete "Bible" the only credible source of belief, as well as others with new attempts to further distort the traditional message by using modern academia to establish yet another scriptural canon, more amenable to their agenda.Specifically, I refer to a group calling itself "The Westar Institute" which is responsible for a contemporary project they call "The Jesus Seminar." Claiming religious literacy as their goal, they vote on what they consider to be believable.

That is why our holy God-bearing Fathers appointed feasts prepared for by fasts to be observed in cycles, yielding the right interpretation of texts they had approved as being authentic scripture. We must repent of our selfishness to receive matching inspiration to faithfully copy the whole package, which they had been inspired to approve, as being inspired by all who wrote correctly about God's immutable purpose. As our Saviour Jesus Christ told His cousin St. John, "Let it be so now; for it is proper for us in this way to fulfill all righteousness." (Mat. 3:15)

St. Paul's letter to Titus, reminds us that "…when the goodness and loving-kindness of God our Saviour appeared, he saved us, not because of any works of righteousness that we had done, but according to his mercy, through the water of rebirth and renewal by the Holy Spirit." Lest any fall into that classical trap of imagining that salvation is only a mind game, that requires no sweat equity, St. John's 1st General Epistle reminds us of the response expected from each of us, in the time that God gives us, "Who is it that conquers the world but the one who believes that Jesus is the Son of God?" John, the Theologian, goes on to list important signs of true belief. In Luke 3:22, that author answers by referring the reader to the fullness of testimony, to which we have been called and should share, by all of our works. It can be transmitted, only by faithfully demonstrating that what we believe to be the absolute truth, was revealed By God the beloved Son. He came to become one of us, leading us, that we might, by everything that we do, proclaim Him as "Lord of all."

Abba Thomas

## <u>አጫጭር ዜናዎች</u>

ሰለ ቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎትና እንቅ ስቃሴን በተመለከተ በከተማችንና በመላው ዓለም ያሉ ምዕመናን ይረዱ ዘንድ በማሰብ የቤተ ክርሰቲያናችን ዌብ ሳይት በአዲስ መልክ እንደገና ተዘጋጅቶ በDec 6, 2008 አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።
http://www.msmedhanealem.org

---

ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የምስጋና ቀን በሚል የተዘጋጀው ልዩ ፐሮግራም ብዙ ምዕመናን በተገኙበት Oct 20, 2008 ቀን ተከብሮ ውሏል። በዕለቱም ምዕመናኑ በአንድነት በርከት ያሉ ያሬዳዊ ዜማ ያላቸው መዝሙሮች ን ሲዘምሩ አምሽተዋል።

---

በየዓመቱ በቤተ ክርስቲያናችን የሚከበረ ው የመስቀል በዓል ዘንድሮም Sep 28, 2008 ቀን ብዙ ምዕመናን በተገኘበት ተ ከብሮ ውሏል። በዕለቱም አባትና እናቶ ች፣ ወጣቶች እንዲሁም የሕጻናት መዘ ምራን የተለያዩ ያሬዳዊ ዜማዋችን ያቀረ ቡ ሲሆን፤የችቦ ሥርዓት ከተካሄደ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል።

---

የቤተ ክርስቲያናችን ዓመታዊ ጠቅላላ ስ ብሰባ Dec 7, 2008 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲ ያኖ የጽዮን አደራሽ ተከናውኖል። በዚ ሁ ስብሰባ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ የውስጥ ኦዲተርስ ዘገ ባ ለሕዝብ ቀርቦል። በዚሁ ዕለትም ለሚ ቀጥሉት ሁለት ዓመታት ኦዲተርስ ሆነ ው ሊያገለግሎ የሚችሉ ግለሰቦችን የሚ ያስመርጥ 3 አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሜቴ የተመረጠ ሲሆን የቤተ ክርስቲያ ኗ ንብረት የሆነውን Skyline ላይ የሚገ ኘውን መሬት በተመለከተ ጥናት አጥንተ ው እንዲያቀርቡ በማለት 5 አባላት ያሉ ት ኮሜቴን ጥቅላላው ስብሰባ አቋቁሟል። ይህ ኮሜቴ ጥናቱን በ3ወር ጊዜ ውስጥ አጠናቆ እንዲያቀርብ ሲል ጠቅላላው ጉ ባኤ ውሳኔ አስተላልፎ ተለያይቷል።

---

በየዓመቱ በሕጻናት ስንበት ት/ቤት በጥሩ መልክ እየተቀነባበረ የሚቀርበው የጌታን ልደት የሚያሳይ ድራማና መዝሙር ዘን ድሮም Dec 20,2008, 5 - 7pm
በቤተ ክርስቲያናችን አዳራሽ ብዙ ምእ መናን በተገኙበት ታይቷል።

---

የቤተ ክርስቲያኗ ፈንድሬዚንግ ኮሜቴ በአዘጋጀው የገንዘብ ማስባሰቢያ ምሽት ላይ ከመቶ ሺ ዶላር በላይ ለቤተ ክርስ ቲያኖ በማስባስብ ገቢ ለማድረግ ተችሏ ል።

## ጠይቁን እንመልሳለን

ይህ ዓምድ ከምዕመናን የሚጠየቁ ጥያቄዎችን የምናብራራበት፣ መልስ የምንሰጥበት ነው።

*ጾም ማለት ምን ማለት ነው?*

(ጠያቂ ወ/ሮ አልማዝ)

ጾም (ጦም) ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል መወሰን ማለት ነው። ወይም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጐመዡውን ነገር መተው ማለት ነው። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውሃ ባፋቸው አይገባም ነበር። በኃጢአት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር። በሐዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራ መጀመሪያ አድርጎ የሥራው ሕግ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር መንፈስ ርኩስ ሰይጣን እንኳ በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኃኒታችን ተናግሯል። ቤተ ክርስትያን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እንዳሉ ነበር። ለሰብከተ ወንጌል የሚያገለገሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነበር። እነ ቆርኔሌዎስ ያላሰቡትን ያዩና ያገኙት በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው። ጾም የታሪክ ድርጊቶችን እያሰታወሱ ከሃጢአት ለመንጻት ሰለራስ የታሰበውን ለነዳያን መሰጠት የሚጾም መሆኑን ተረድተናል። ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጾማል። «ለሚያሳድዱህ ጹምላችው» እንደ ተባለ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን ፣ በሰደትና በምርኮ ያሉትንም በጾም ወራት ማሰታወስ መጸለይ ይገባል። በጾም ወራት ከመባልዕት መወሰን ብቻ ሳይሆን ዓይን ክፉ ከማየት፤ አንደበት ክፉ ከመናገር፤ የተቀጠበ እንደሆነ ጾሙን ክርስቲያናዊ ያደርገዋል።

## ይህን ያውቁ ኖሯል? (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚያም አልፎ ሀገራችን ሰፊ በመሆኗ ተጨማሪ ጳጳሳት እንዲላኩና ኢትዮጵያውያንም ለዚህ ደረጃ እንዲበቁ ጥያቄ ከማቅረብ አልተቆጠቡም።

ከዛጔዌ ሥርወ መንግሥት ከነገሡት መኻከል በጣም ታዋቂ የነበሩት ይምርሃነ ክርስቶስ (ከ1077 - 1117 ዓ.ም) እና ላሊበላ (ከ1157 - 1197 ዓ.ም) ናቸው። ይምርሃነ ክርስቶስ አስማትና ጥንቆላ እንዲሁም አንድ ሰው ከአንድ በላይ እንዳያገባ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቃል ራሱን አርአያ በማድረግ ሕግ የደነገገ ነው። በተለይ ላሊበላ በአንድ አካባቢ ያነጻቸው እስካሁን የሚታዩት ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩት 11 አብያተ ክርስቲያናት ዓይነተኛ ምስክሮች ናቸው። በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶችም ተመሳሳይ አብያተ ክርስቲያናት አሳንጿል። ላሊበላ ያሠራቸው እነዚህ ድንቅ የሆኑ ሕንጻዎች በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ ታሪካዊ ቅርሶች ተብለው ተመዝግበዋል። ለትልልቅ ገዳማት መመሥረትና የክርስትና እምነት ከዚያ ቀደም ባልደረሰባቸው ቦታዎች እንዲዳረሱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ኢየሱስ ሞዐ እና በኋላ ቅዱስ የተባሉት ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያ ስማቸው ፍስሐ ጽዮን የተወለዱት በዚሁ በበዛጔ ሥርወ መንግሥት ጊዜ ነው። በዐፄ ነአኩቶ ለአብ ዘመነ መንግሥት ለረጅም ጊዜ ጳጳስ ካለመኖሩ የተነሣ የካህናት ቁጥር በጣም እያነሰ በመምጣቱ ንጉሡ ካህናቱን ሰብስበው ጳጳስ እስኪመጣምን ማድረግ እንዳለባቸው ከተወያዩ በኋላ ከመሐከላቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጊዜያዊነት ጳጳስ እንዲሆኑ አደረጓቸው። አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ኢየሱስ ሞዐ (1203-1284 ዓ.ም) ከሐዋርያዊ ተልዕኮአቸው ባሻገር ሥርወመንግሥቱ ከዛጔ ወደ ሰሎሞናዊ በሰላም እንዲሻገር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የዛጔ ሥርወ መንግሥትም ለ333ዓመታት ከቈየ በኋላ ሥልጣኑን ይኩኖ አምላክ ጨበጠ፤ መቀመጫውንም በሸዋ ተጉለት አደረገ (1263-1278 ዓ.ም)።

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

## ከቅዱሳት መጻሕፍት

(ከቅዱስ ዲዮስቆሮስ ቅዳሴ የተወሰደ)

ሰማይ ይስማ ምድርም ታድምጥ፤
የምድር መሰረቶችም ይደንግጡ።
በአባቱ ፈቃድ ወረደ፤
በማርያም ዘንድ እንግዳ ሆነ እግዚአብሔር በንጹሕ ድንግልናዋ ተወለደ።
በእንስሳት በረት ተጨመረ፤
የንጉሱንም እጅ መንሻ ተቀበለ፤
ከእናቱም ጡቶችን እየለመነ እንደ ሕፃናት አለቀሰ።
በግልጥ ተመላለሰ እንደ ሰውም ታየ፤
በየጥቂቱ አደገ በሠላሳ ዘመን በዮርዳኖስ ተጠመቀ።

## The Anaphora of St. Dioscorous.

Let heaven hear, the earth listen; and the foundations of the earth be afraid.
The Lord came down through the will of His Father, sojourned in Mary and was born while she was a pure virgin. He was laid in the manger of the cattle, received the presents of His kingdom, and wept as infants do, asking for food from the breasts of His mother.
He walked openly and appeared like a man, grew little by little and was baptized in Jordan at the age of thirty.

## ተወለደ

ሰዎች እልል በሉ ምስራች ተሰማ
ከቤተልሔም ዋሻ ከዳዊት ከተማ
ለአዳም አባታችን ቃል እንደገባለት
አበው በአደባባይ እንደተናገሩት
ተወልዶ ሊያድነው ከኃጢአት ባርነት
ይኸው ተወለደ ጌታችን በበረት።
በድንግል ማሕጸን ሆነ ተዋሕዶ
የሰውን ሥጋ ለብሶ አማኑኤል ተወልዶ
በዓለም ይሰማ ይህ ታላቅ ዜና
የምድር ጠቢባን ይሰገዱ ይምጡና
የተወለደልን መድኃኒት ነውና።
የውልደቱ ዜና ሲሰማ በሁሉም
መላዕክት ሲያውጁ ምስራች በዓለም
ይዘውለት መጡ የእጅ መንሻ ነገሥታቱ
ወርቁን አቀረቡ ለንጉሥነቱ
ከርቤንም አመጡ ለመራራ ሞቱ
ዕጣን አቀረቡ ለክህነቱ
ይህ ታምር ሲሰማ በኢየሩሳሌም ሀገር
ሄሮድስ ደነገጠ ከነሠራዊቱ ፈጠረ ሽብር
መስሎት ሰለነበር ለምድራዊ ክብር
በምድር የታየው ጌታ መድኃኒት
ለጠፋነው ሁሉ ሊሆን ነው ሕይወት።
ተነሱ እንሂድ ሁላችን ልደት
ተጠርተናል እና ከናታችን ቤት
ተትረፍርፎ ሞልቷል ማርና ወተት።
የሚፈለግብን የመግቢያው መስፈርት
እራስን አንፅቶ ብቻ መገኘት።

*ከሃይማኖት ገ/ሥላሴ*

## መጪ ዝግጅቶች

በየዓመቱ የሚከበረው የገና በዓል ዘንድሮም በደመቀ ሁኔታ ታህሳስ ፳፱ (Jan 7) በመላው የኦርቶዶክ እምነት ተከታዮች ተከብሮ ይውላል። በበዓሉም ዋዜማ (ታህሳስ ፳፰) ቤተ ክርስቲያናችን ከምሽቱ 6 PM ጀምሮ ለአገልግሎት ክፍት ይሆናል።ይህን ታላቅ የጌታ ልደት ቀን ሁላችንም በአንድነት ሆነን እንድናከብር ቤተ ክርስቲያን ትጋብዛለች።

---

ጥር ፱ - ፲ (Jan 17-18, 09) የጥምቀት በዓል በሎሳንጀለስ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ብዙ ምዕመናን በሚገኙበት ተከብሮ ይውላል።

---

መዝሙረ ተዋሕዶ በሚል የሚወጣው ተከታታይ የመዝሙር ሲዲ (ቁጥር ፬ን፣ የጥምቀት በዓላትን የተመለከተ) በቤተ ክርስቲያናችን መዘምራን በቅርብ ቀን በገበያ ላይ ይውላል።

## ፍቅርን እንወቅ!

ሐዋርያው ዮሐንስ በ፩ኛ መልእክቱ በምዕራፍ አራት ቁጥር አንድ ላይ በዚህ ዓለም ውስጥ ብዙ እውነተኛ መንፈስ ነን ባዩች (ሐሰተኛ ሆነው ሳለ) እንደሉና እንደሚያስቱ ይናገራል። በዚሁ ቁጥር ላይ የሐሰተኛን መንፈስና የእግዚአብሔርን መንፈስ ልንመረምርና ለይተን ልናውቅ እንደሚገባን ያስገነዝበናል። የክርስቶስን በሥጋ መምጣት የማያምን መንፈስ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ልናውቅ ይገባል። የክርስቶስን በሥጋ መምጣት የማይቀበል መንፈስ የክርስቶስ ተቃዎሚ እንጂ እውነተኛ መንፈስ አይደለም ማለት ነው።

ዮሐንስ በዚሁ ምዕራፉ በቁጥር አራት ላይ እኛ እውነተኛውን መንፈስ ካወቅንና የእግዚአብሔር ከሆንን ዓለምንም ሆነ በውስጧ ያለውን ሐሰተኛ መንፈስ እንደምናሸንፍ ይነግረናል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ከመወደዱ የተነሳ (ፍቅሩ አስገድዶት) እራሱን ለእኛ ሲል ለሞት አሳልፎ ሰጠ። እኛም እግዚአብሔር እኛን በወደደን መውደድ እርስ በርሳችን እንድንዋደድና እርሱን እንድንመስል ይነግረናል። እግዚአብሔር ሰውን ከሞት ወደ ሕይወት የመለሰው እንዲሁ ሳይሆን አንድያ ልጁን አሳልፎ በመስጠት ነው። (1ኛ ዮሐ. ም. 4፥9)

እንግዲህ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጐ ከውደደንና እራሱን አሳልፎ ከሰጠን እኛስ አብረውን የሚኖሩትን ወንድሞቻችንን እንዴት አንወዳቸውም?



ጌታ በዚች ምድር ላይ በሥጋው በተመላለስ ጊዜ፣ እርስ በርሳችን ከተዋደድን እግዚአብሔር በመካከላችን እንደሚገኝና በበረከት እንደምንሞላ አስተምሮናል። ዮሐንስም በምዕራፍ አራት ቁጥር አሥራ ሦስት እስከ ሃያ አንድ፣ ክርስቶስም እውነተኛውን መንፈስ እንደሰጠንና እርሱም በእኛ እንደሚኖር የክርስቶስም መከራን መቀበል ለእኛ ሕይውት እንደሚሆንና ልጆችም እንደሚያደርገን ይነግረናል።

እኛም በእግዚአብሔር ታምነን ከኖርን እግዚአብሔር ደግሞ በእኛ ይኖራል። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንም ተቀብለነዋል። እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ አውቀናል ፍቅርም ሕይወትን በመስጠት ከእኛ ጋር አንድ ሆኖል፣ ተፈጽሟል ማለት ነው። (ም. 4፥17)

ፍቅር ፍርሃትንም ሆነ የክፉ መንፈስ ጥርጣሬን ያስወግዳል። ፍርሃት ከደካማ መንፈስ፣ የእግዚአብሄርን መንፈስና የክፉ መንፈስን፣ ለይቶ ከአለማወቅ የሚመጣ ነው። ፍቅር ያለው ግን እግዚአብሔር አለው! በፍርሃት በክፉ መንፈስ ወይም በኃጢያት ሊናወጽ አይችልም። በውስጡ የእግዚአብሔር ፍቅር አለና። (ም. 4፥16)

ማንም የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ከሆነ ያላየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወድ ይችላል? በመጀመሪያ ክርስትናም ሆነ መንፈሳዊ ነገር የሚጀምረው ከቤተሰብ ወይም ከእህት ከወንድም፣ ከእናት ከአባት፣ … ነው። ማንም እግዚአብሔርን የሚወድ ከሆነ ወንድሙን ወይም ባልንጀራውን ሊወድ ይገባል። ካለበለዚያ ፍቅርን ወይም እግዚአብሔርን ገና አላወቀም ማለት ነው። ም. 4፥20-21፤ 1ቆሮ ም. 4

ጌታ መድኃኔዓለም ፍቅርን ለማናውቅ ሰዋች እግዚአብሔር ፍቅርን እንድናውቅ ይርዳን። አሜን!

መንበረ
ከአትላንታ ጆርጂያ

## ዝክረ ምኒልክ ወጣይቱ

አጤ ምኒልክ የውጫሌ ውልን የማይቀበሉት መሆኑን ለጣልያን መንግሥትና ለሌሎቹ የአውሮፓ መንግሥታት ከመጀመሪያው ጀምሮ ቢያስታውቁም ሰሚ ስላጡ የስምምነቱ ጊዜ አስኪያበቃ ጠበቁ። በ1888 አጤ ምኒልክ መኳንንቱን ሰብስበው ስለጣልያን ዘመናዊ መሣሪያና ገናንነት መንገር ትታችሁ ለጦርነት ተዘጋጁ። ኃይል ከእግዚአብሔር ነውና እኔም የሀገሬን ጠላት እጋጠማለሁ ብለው የክተት አዋጅ አውጀው ዘመቱ።

ምኒልክም የተማመኑበት አምላክ ረድቷቸው የካቲት 23 ቀን 1888 ወራሪውን ጦር ድል አደረጉ። ድል ባደረጉ በወሩ በመጋቢት 23 ቀን ለአውሮፓዊው ዲፕሎማት ለሙሴ ሽፍኔ እንዲህ በማለት ጻፉለት _«በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ። እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርሲቲያን ደም መፍሰስ እያየሁ ድል አደረኩኝ ብዬ ደስ አይለኝም»_

አስተያየትና ጥያቄ ካላችሁ ወይም ደግሞ ጽሑፎቻቹህ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉ ካላችሁ በቤተ ክርስቲያኒቷ የአስተያየት መስጫ ያኑሩልን። ወይም ደግሞ በሚከተለው የሥነ ጽሑፍ ዝግጅት ክፍል ኢሜይል ይላኩልን።
hamere_noh@yahoo.com

**የቤተ ክርስቲያን መደበኛ አገልግሎቶች**

ዘወትር እሁድ ጠዋት ከ7:00 - 12:00 የቅዳሴ፣ ስብከትና መዝሙር አገልግሎት ይካሄዳል።

ከ12:15 - 1:00 በሰንበት ት/ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የመዝሙር መርሐ ግብር ይካሄዳል።

ዘወትር ዕሮብ እና ዓርብ ማታ ከ6:00 - 8:00 የሠርክ ጸሎትና የመጸሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይካሄዳል።

ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት፤ የሠርግ፣ የክርስትና፣ የፍትሐት አገልግሎትን ለምትሹ በ 510 336 1168 ደውለው ያነጋግሩን።